# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2016/13*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ በሶማሌ ክልል ለተደረገ የፋይናንስ አገልግሎት ማስፋፊያ ድጋፍ ሰጠ

*መጪውን ትውልድ መመገብ ከተሰኘው የአሜሪካ መንግሥት መርሀ ግብር በተደረገለት ድጋፍ፤ ሄሎ ካሽ የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎቶችን ይሰጣል*

***ጅጅጋ፣ኢትዮጵያ፣ የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ.ም.*፡-** በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ፓትሪሺያ ሃስላክ የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ.ም. የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት የተከበሩ አቶ አብዲ መሐሙድኑር ኦማር በተገኙበት የሄሎ ካሽ አገልግሎት በይፋ መርቀው ከፈቱ፡፡

የአሜሪካ መንግሥት ከሶማሌ ክልላዊ መንግሥት የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ጋር በመተባበር በክልሉ የተጀመረው ይህ የሄሎ ካሽ አገልግሎት በሞባይል ባንኪንግ ዘርፍ የሚንቀሳቀስ ነው፡፡ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ብቻ 780,000 የሚሆኑ የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ወደ 12 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በብድር፣በቁጠባ እና በሐዋላ አገልግሎቶች ያንቀሳቅሳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም የፋይናንስ አገልግሎቱ 2,000 ለሚሆኑ አባወራዎች በወኪልነት፣በአገናኝነትና በአቅራቢነት የሥራ ዕድል ሊፈጥር እንደሚችል ተጠቁሟል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ለሄሎ ካሽ ያደረገው ድጋፍ በሜርሲ ኮር (Mercy Corps) ከሚተገበረው ለአርብቶ አደሩ የገበያ ዕድሎችን በማስፋት አቅሙን መገንባት ላይ ያተኮረው የኤጀንሲው መርሀ ግብር ነው፡፡ ኤጀንሲው ከተደራሽነት አኳያ እጅግ አስቸጋሪ የሆኑ አካባቢዎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ የ350,000 ዶላር የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል፡፡ በሌላ በኩልም የክልሉ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም 3 ሚሊዮን ዶላር የመደበ ሲሆን፤ ቤል ካሽ የተሰኘ ድርጅት በበኩሉ 1.8 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ሊያደርግ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክም ባለፈው ዓመት የክልሉ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ይህንን አገልግሎት ይሰጥ ዘንድ ይሁንታውን ሰጥቷል፡፡

አምባሳደር ፓትሪሺያ ሃስላክ ስለ አዲሱ አገልግሎት በተናገሩበት ወቅት፡-“ይህ አዲሱ የፋይናንስ አገልግሎት በሶማሌ ክልል መጀመሩ እጅግ አስደሳች ነው፡፡ አገልግሎቱ የሥራ ፈጠራን ከማበረታታቱም በላይ፤ በአሥርት ሺዎች የሚቆጠሩ አባወራዎችን ገቢ የሚያሳድግ ይሆናል፡፡” ብለዋል፡፡

የዚህ የሄሎ ካሽ አገልግሎት ድጋፍ የተገኘው ከአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ፣ ሜርሲ ኮር ከሚያስተዳድረው የፈጠራና የመዋዕለ ንዋይ ፈንድ ሲሆን፤ የፈንዱ ዓላማ የአርብቶ አደር አባወራዎችን ገቢ ማሳደግና አደጋን የመቋቋም አቅማቸውን መገንባት ነው፡፡ ከዚህም አኳያ በየአካባቢው ያለውን ካፒታል በመጠቀም የገበያ ትስስርን በመፍጠር፣ የሥራ ዕድሎችን

በማመቻቸት እና ሁሉን-አቀፍ የፋይናንስ ሥርዓት ተጠቃሚነትን በመዘርጋት ላይ ያተኮሩ የተለያዩ የገበያ ልማት እንቅስቃሴዎችን በማካሄድ ላይ ያተኩራል፡፡

###

###